የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

(ከህዳር 17- 23/2017 ዓ.ም)

(25 Nov- 2 Dec, 2024)

## 1.አስመጪዎች ዕቃ ባስገቡበት ዓመት ሪፖርት ተደርጎ ያልተከፈለ ቅድመ ግብር ወለዱን ጨምሮ እንዲከፈል ትዕዛዝ ተሰጠ

*ሪፖርተር፡ December 1, 2024*

የጉምሩክ ኮሚሽን በገቢ ግብር ሕጉ ድንጋጌ መሠረት ዕቃ ወደ አገር ውስጥ በገባበት ዓመት የንግድ ሥራ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ያልተከፈለ ከሆነ፣ በድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ጊዜ ቅድመ ግብሩ ወለዱን ጨምሮ እንዲከፈል ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡

የቅድመ ግብር ክፍያ (Withholding Tax) ክፍያ መከፈል እያለበት ሳይከፈል ዕቃ ወደ አገር በሚገባበት ጊዜ በጉምሩክ ድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት በኩል ክፍያ መኖሩ ተረጋግጦ አስመጪዎች ክፍያ እንዲፈጽሙ መጠየቃቸውን የገለጸው ኮሚሽኑ፣ ዕቃው በገባበት ወቅት ለጉምሩክ ያልተከፈለ ቢሆንም ግብር ለሚከፍሉበት መሥሪያ ቤት በዓመታዊ ትርፍ ግብር ላይ ተካቶ የተከፈለ ስለሆነ በድጋሚ ልንጠየቅ አይገባም በማለት አስመጪዎች ለኮሚሽኑ ተደጋጋሚ አቤቱታ ማቅረባቸውን አስታውቋል፡፡

ጉዳዩን በተመለከተ ለገቢዎች ሚኒስቴር ማብራሪያ እንዲሰጥበት መጠየቁን ያስታወቀው የጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለጥያቄው የገቢዎች ሚኒስቴር የሰጠውን ዝርዝር ማብራሪያ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ማስተላለፉን ገልጿል፡፡

በማብራሪያው መሠረት የድኅረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተደረገው ዕቃው በገባበት የግብር ዘመን ያለው የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ሪፖርት ተደርጎ ከተከፈለ በኋላ ከሆነ፣ በግብር ሕጉ መሠረት ሊካካስ ስለማይችል ቅድመ ግብሩ አይከፈልም፡፡ ነገር ግን ኮሚሽኑ ዕቃው ወደ አገር ከገባበት ቀን እስከ የግብር ዘመኑ የንግድ ሥራ ግብር ቀን ድረስ ወለድ ሊከፈል ይገባል ሲል አክሏል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135947/

## 2. በፍራንኮ ቫሉታ ግዥ የፈጸሙ አስመጪዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የንግድ ሸቀጦችን እንዲያስገቡ ማሳሰቢያ ተሰጠ

**ሪፖርተር፡ December 1, 2024**

ከጥቅምት 28 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት የንግድ ሸቀጦችን በፍራንኮ ቫሉታ ግዥ ፈጽመው ሰነዳቸው የተረጋገጠላቸው አስመጪዎች፣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የንግድ ሸቀጦቻቸውን አጠቃለው ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ የጉምሩክ ኮሚሽን አሳሰበ፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በውጤታማነት ተግባራዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግና በአጭር የሽግግር ጊዜ ሊፈጠር ይችል ነበረውን ዋጋ ንረት ለማስቀረት፣ ተግባራዊ ተደርጎ የነበረው የንግድ ሸቀጦችን በፍራንኮ ቫሉታ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት አሠራር ከጥቅምት 28 ቀን ጀምሮ መሰረዙን ማስታወቁ ይታወሳል፡፡

በፍራንኮ ቫሉታ ግዥ የተፈጸመባቸው የንግድ ሸቀጦች ካሉ ከጥቅምት 28 ቀን ጀምሮ በሁለት የሥራ ሳምንታት ውስጥ ሕጋዊ ሰነዶች ለጉምሩክ ኮሚሽን ቀርበው፣ ተቀባይነት በማግኘት፣ የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልተው ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የገንዘብ ሚኒስቴር ትዕዛዝ አስተላልፎ ነበር፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135958/

## 3. በሀገሪቱ ጤናማ የግብይት ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ ተግባራት በቅንጅት እየተከናወኑ ነው --ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)

**ኢዜአ፡ ህዳር 22/2017**

በሀገሪቱ ጤናማ የግብይት ስርዓትን በመፍጠር የኢትዮጵያን ገቢ ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት በቅንጅት እየተከናወኑ እንደሚገኝ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ገለጹ።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኮምቦልቻ ከተማ በ85 ሚሊዮን ብር ያስገነባው ዘመናዊ የምርት ማከማቻ መጋዘን ተመርቆ ለአገልግሎት ዝግጁ ተደርጓል። ሚኒስትሩ ዶክተር ካሳሁን ጎፌ እንደገለፁት፤ ጤናማ የግብይት ሰንሰለትና ስርዓትን በመፍጠር የኢትዮጵያን ገቢ ለማሳደግ በቅንጅት እየተሰራ ነው። በተያዘው በጀት ዓመትም ከወጪ ንግድ 6 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እየተተገበረ ሲሆን በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በተደረገ እንቅስቃሴ ከ2 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ገልፀዋል።

በተለይ ህገወጥ ንግድንና ህገወጥ ኬላዎችን በመከላከል ምርት በነጻነት መንቀሳቀስ እንዲችልና ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን እየተሰራ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የተለዩ 283 ህገወጥ ኬላዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ይህም የተሳለጠ የግብይት ስርዓት እንዲኖር መስተካከል ይኖርበታል ብለዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5552486

## 4. ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እምቅ አቅም ያለው የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ዘርፍ

**Ethiopian Press: November 28, 2024**

የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ በአስር ዓመት ሀገራዊ እቅድ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱና ዋናው ሲሆን፤ እሴት በመጨመር፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ ኤክስፖርት በማድረግ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት እና ገቢ ምርቶችን በመተካት ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ዘርፍ ነው:: ይህ ዘርፍ ፈትል (ድርና ማግ፣ ክር እንዲሁም የተሸመኑና የተገመዱ ጨርቃ ጨርቆችን ማምረትን፤ ጣቃ ጨርቅን፣ ክርን፣ ድርና ማግን፣ አልባሳትንና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣት፣ በማቅለም፣ በማኮማተር፣ በማፍካት፣ በማጠንከር ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅን፤ አልባሳት (የስፖርት ልብስን ጨምሮ)፣ ሹራብ፣ ፎጣ፣ ምንጣፍ፣ ተጓዳኝ አካላትን (ቁልፍ፣ ዚፕ… ማምረትን ያጠቃልላል::

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ዘርፉን ለኢንቨስትመንት ተመራጭ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል፤ ከግብርና ጋር ተመጋጋቢ የሆነና በቂ የሆነ የግብዓት ሀብት መኖር፤ ዘርፉ ውስብስብ ያልሆነና ወደቀጣይ ሥራ ሊያሸጋግር የሚችል ቴክኖሎጂ የሚጠቀም እንዲሁም እርስ በእርስ ሊተሳሰር የሚችል መሆኑ፤ በቀላሉ ሊሰለጥን የሚችል የሰው ኃይል እና ከፍተኛ የሀገር ውስጥና የዓለም ገበያ መኖሩ እና በመንግሥትና በግል ባለሀብቶች የተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ክላስተሮች መኖራቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ::

በዚህ ዘርፍ ከሚመረቱ ምርቶች መካከል ከተልባ እግር ክር የሚሰራው የአልባሳት ውጤት የሆነው ሊነን ቴክስታይል (Linen Textile) ይጠቀሳል:: ኢትዮጵያ ተልባ የማምረት ትልቅ አቅም ያላት ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ከዚህ ተክል የሚመረተው የአልባሳት ምርት ጥቂት ከመሆኑ ባሻገር ምርቱ ሙሉ በሙሉ ለውጭ ሀገራት ገበያ የሚቀርብ ነው::

https://press.et/?p=141759

**5. AfCFTA Unique Opportunity to Strengthen Regional Integration, Enhance Industrialization**

**ENA: November 30/2024**

Innovative policies and robust partnerships are key for Africa to overcome the challenges facing the implementation of the African Continental Free Trade Agreement (AfCFTA), experts underscored.

The experts made this remark at a Workshop on Modelling the Impact of AfCFTA on African Economies in Addis Ababa, Ethiopia.

The experts underscored the role of economic modelling in crafting evidence-based policies for the AfCFTA's successful implementation.

The workshop was organized virtually by the Macroeconomics, Finance and Governance Division (MFGD) of the Economic Commission for Africa (ECA) on the theme "Modelling the Impact of the African Continental Free Trade Agreement (AfCFTA) on African Economies

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5544351

**6. Economists forecast GDP growth shrink, inflation bump in 2025**

**The Reporter: November 30, 2024**

A new policy paper published by the Ethiopian Economics Association (EEA) predicts a three percentage point drop in GDP growth and a 10 percentage point rise in the inflation rate over the coming months.

The policy paper, titled '*Initial reflection on the likely effects of Ethiopia's foreign exchange rate reform on macro-economic indicators*', was authored by Yetsedaw Emagne and Tadele Ferede (PhD).

The authors considered the economic outlook based on a reunification scenario, where the official and parallel forex rates would converge, and another featuring a more gradual adjustment scenario.

This first scenario of the study aligns with a central bank statement this week, indicating that the reform's immediate impacts include a sharp reduction in the parallel market premium, which fell from nearly 100 percent to near five percent.

https://www.thereporterethiopia.com/42777/

**7. PACCI Calls for Adjustments to Ensure Africa's Economic Growth**

**Capital: December 2, 2024**

As the US Senate deliberates the AGOA Renewal and Improvement Act of 2024, extending the African Growth and Opportunity Act (AGOA) until 2041, the Pan-African Chamber of Commerce and Industry (PACCI) has raised critical concerns. While the 16-year extension offers stability for Africa-US trade relations, PACCI emphasizes the need for greater flexibility to ensure the legislation benefits African economies without creating undue barriers.

The new legislation proposes several updates to AGOA, including enhanced eligibility criteria, stricter compliance standards for textile exports, and provisions to align with regional integration efforts under the African Continental Free Trade Area (AfCFTA). However, these changes come these changes come with potential risks for African exporters.

Kebour Ghenna, Executive Director of PACCI, applauds the extension but cautions against provisions that may unintentionally exclude countries or create compliance bottlenecks.

https://capitalethiopia.com/2024/12/02/revisiting-agoa-pacci-calls-for-adjustments-to-ensure-africas-economic-growth/

**8. AFCAC Honors Ethiopian Airlines for Its Significant Contributions to African Aviation**

**ENA: December 2/2024**

Ethiopian Airlines has been honored by the African Civil Aviation Commission (AFCAC), the African Union's specialized agency for civil aviation, for its significant contributions to African aviation.

The airline received recognition as the Airline with the Most Intra-Africa Routes during the triennium 2022–2024 at the 35th AFCAC Ordinary Plenary Session held in Brazzaville, Republic of Congo.

AFCAC honored the Ethiopian Airlines for its exemplary leadership, unwavering commitment, and significant contributions to African aviation.

Additionally, Addis Ababa Bole International Airport, Ethiopian's main hub, was acknowledged as the Airport with the Highest Volume of Intra-Africa Traffic for the same period.

The AFCAC Plenary, convened once every three years as mandated by its constitution, serves as the supreme decision-making body of the African Civil Aviation Commission.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5554767